# የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት

## የአገልግሎት አቅርቦት የክፍያ ሥርዓት መመሪያ ቁጥር 01/2017

ሐምሌ 2017 ዓ.ም

<u>አዲስ አበባ</u>

# <u>ማውጫ</u>


መግቢያ ......................................................................................................3

ክፍል አንድ ..................................................................................................4

ጠቅላላ ድንጋጌ ..............................................................................................4

1. **አጭር ርዕስ** ..........................................................................................4
2. **ትርጓሜ** ..................................................................................................4
3. **ዓላማ** ....................................................................................................5
4. **የተፈጻሚነት ወሰን** ..................................................................................5

ክፍል ሁለት ..................................................................................................5

ስለክፍያ ተመን አወሳሰን ሥርዓት ..........................................................................5

5. **የክፍያ ተመን አወሳሰን መስፈርቶች** ..............................................................5
6. **የክፍያ ትመና ሥርዓት** ..............................................................................5
7. **የክፍያ ተመን ስለመከለስ** ..........................................................................6
8. **የክፍያ አፈጻጸም** ....................................................................................6

ክፍል ሶስት ..................................................................................................7

ስለተግባርና ኃላፊነት ........................................................................................7

9. **የኢንስቲትዩቱ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት** .....................................................7
10. **የክፍያ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት** ............................................................7

ክፍል አራት ..................................................................................................7

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች ........................................................................................7

11. **ክልከላ** ..................................................................................................7
12. **ተጠያቂነት** .............................................................................................8
13. **የመተባበር ግዴታ** ....................................................................................8
14. **መመሪያውን ስለማሻሻል** ............................................................................8
15. **መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ** ........................................................................8


ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር


በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Biodiversity Institute

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ለሀገራችን የተፋጠነ ዕድገት መሠረት የሆነውን የብዝሀ ሕይወት ሀብትና ተያያዥ የማህበረሰብ ዕውቀት በምርምር በተደገፈ አሠራር በተገቢው መንገድና በተፈለገው ልክ ታውቆ እንዲነበር፤ አሁን ያለው የብዝሀ ሕይወት ሀብት በመጠን፣ በስርጭትና በተለያይነት እንዲጨምር የሚያስችል ዘለቄታዊ አጠቃቀም እንዲተገበር እና ከብዝሀ ሕይወት የሚገኝ ጥቅም ሚዛናዊና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የማህበረሰብ ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ እየሠራ ያለ ተቋም በመሆኑ ፤

ተቋሙ የሚሰጣቸው አገልግሎቶች እስከ ማህበረሰብ ደርሰው የሚፈጸሙ በመሆናቸው አሠራራቸው ግልጽነትና ወጥነት ያለው እንዲሆንና ለሚሰጠው አገልግሎት ተገቢውን ክፍያ ማስፈጸም አስፈላጊ መሆኑ በመታመኑ፤

ተገቢውን የአገልግሎት ክፍያ ተመን ስርዓት በማዘጋጀት ሀገራችን ከብዝሀ ሕይወት ሀብት ማግኘት የሚገባትን ምጣኔ ሀብታዊና ማህበራዊ ጥቅሞች እንድታገኝ በማስፈለጉ፤

በተጠና እና በተቀናጀ መንገድ የሚወሰን የአገልግሎት ክፍያ ትመናን መዘርጋትና ወጥ፣ ግልጽና ፍትሃዊ የክፍያ ስርዓትን መተግበር በማስፈለጉ፤

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱትን ለማሳካትና ውጤታማ ለማድረግ ይረዳ ዘንድ የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩትን ለማቋቋም በወጣው የሚንስትሮች ም/ቤት ደንብ ቁጥር 291/2005 አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 25 መሠረት ይህ የአገልግሎት አቅርቦት የክፍያ ሥርዓት መመሪያ ተዘጋጅቷል።

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ "የአገልግሎት አቅርቦት የክፍያ ሥርዓት መመሪያ ቁ 01/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. **"ኢንስቲትዩት"** ማለት የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ዋና መስሪያ ቤትንና በስሩ የሚገኙ ቅርንጫፍ የብዝሀ ሕይወት ማዕከላትን፣ የዕፅዋት አፀዶችንና የብዝሀ ሕይወት ዱፕሊኬት ጅን ባንክ ያጠቃልላል።
2. **"የኢንስቲትዩቱ አስተዳደር"** ማለት የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር፣ ም/ዋና ዳይሬክተር፣ መሪ/ዋና ሥራ አስፈፃሚዎች እና ጽ/ቤት ኃላፊ ማለት ነው።
3. **"የክፍያ አስፈጻሚ"** ማለት ኢንስቲትዩቱ ለዚህ ተግባር ሲባል ኃላፊነት የሚሰጣቸው የተቋሙ አካላትና የሚመድባቸው ሠራተኞች ናቸው ።
4. **"ተጠቃሚ"** ማለት ከኢንስቲትዩቱ አገልግሎት ፈላጊና ተቀባይ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው።
5. **"የክፍያ ተመን"** ማለት ለተጠቃሚዎችና ለሌሎች አገልግሎት ፈላጊዎች ለብዝሀ ሕይወት ናሙና፣ ለስልጠናና ለማማከር፣ ለምርምር ግኝት፣ ለአርክቦት ፈቃድ፣ ለጉብኝት፣ ለኪራይ፣ ለፎቶግራፍ፣ ለቪዲዮ እና ለመሳሰሉት አገልግሎት አቅርቦቶች የሚወሰን ዋጋ ነው።
6. **"አገልግሎት"** ማለት በዚህ አንቀጽ ቁጥር 5 ላይ የተዘረዘሩትንና በተቋሙ የክፍያ ተመን የወጣላቸውን አቅርቦቶች የተመለከተ ሲሆን በተጠቃሚዎች ጥያቄ መሰረት የሚሰጥ ነው።
7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።
8. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው ሴትንም ይጨምራል።

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

3. <u>ዓላማ</u>

የዚህ መመሪያ ዓላማ የአገልግሎት ክፍያ ተመን አወሳሰን ወጥ መስፈርቶችን በመከተል፤ በሥርዓት እንዲመራ የሚያስችል ፣ ግልጽና ፍትሀዊ የሆነ አሠራር በመዘርጋት ከብዝሀ ሕይወት ዘርፍ ሃብት ማመንጨት ነው።

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ ኢንስቲትዩቱ በሚሰጣቸው አገልግሎቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

## <u>ስለክፍያ ተመን አወሳሰን ሥርዓት</u>

5. <u>የክፍያ ተመን አወሳሰን መስፈርቶች</u>

በኢንስቲትዩቱ የአገልግሎት ክፍያ ተመን ሲወሰን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች መሰረት በማድረግ ነው፡-

1. የአገልግሎቱን ዓይነትና ስብጥር መለየት፤
2. በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ተመሳሳይነት ያላቸው አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የሚያስከፍሉትን ክፍያዎች ልምድ መቀመር፤
3. የተጠቃሚን የመክፈል አቅም፣ የመክፈል ፍላጎትና የአገልግሎቱን ተፈላጊነት መለየት፤
4. የአገልግሎቱ አስተዳደራዊና የብዝሀ ሕይወት ናሙናን ለመሰብሰብና ለማንበር የሚያስፈልጉ ወጪዎችን ሁሉ በአግባቡ መለየትና በክፍያ መልክ ለተጠቃሚው መተላለፍ የሚገባው መጠን መቀመር ፤
5. የአገልግሎቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታን ከግምት ማስገባት።

6. <u>የክፍያ ትመና ሥርዓት</u>

የአገልግሎት ክፍያ ተመን ለመወሰን የሚከተሉትን ሥርዓቶች መከተል ያስፈልጋል።

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 በተመላከቱት መስፈርቶች ላይ ዝርዝር ጥናት ማካሄድ፤

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

2. የሚመለከታቸውን የኢንስቲትዩቱን አካላት በማሳተፍ ረቂቅ የክፍያ ተመን ዝርዝር ማዘጋጀት፤
3. ረቂቅ የክፍያ ተመኑን በሚመለከተው አካል ማፀደቅ፣
4. የፀደቀውን የክፍያ ተመን የተለያዩ የግንኙነት ዘዴዎች በመጠቀም ለተጠቃሚዎች ማሳወቅ።

7. <u>የክፍያ ተመን ስለመከለስ</u>

1. ኢንስቲትዩቱ ወቅታዊ ሁኔታን በማገናዘብ በማንኛውም ጊዜ የክፍያ ተመን ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል።
2. የክፍያ ተመን ክለሳ ሲደረግ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 5 እና 6 የተመለከቱትን መስፈርትና ሥርዓት መከተል ይኖርበታል።

8. <u>የክፍያ አፈጻጸም</u>

1. ለተጠቃሚ የሚሰጥ አገልግሎት የሚፈጸም ክፍያ እንደ ኢንስቲትዩቱ የገንዘብ አሰባሰብ ሁኔታ በአካል፣ በባንክ እና በኤሌክትሮኒክ የክፍያ ዘዴዎች ሊፈጸም ይችላል።
2. የተጠቃሚዎች የክፍያ ተመን ለሀገራችን ዜጎች እና ተቋማት በብር ሲሆን፤ ለውጭ ሀገር ዜጎች፣ ቆንስላዎች እና ዓለም አቀፍ ተቋማት በአሜሪካን ዶላር ወይም በዕለቱ የምንዛሬ ተመን ብር በባንክ የሚፈጸም ይሆናል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ኖሮ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚቀበላቸው ሌሎች የውጭ ሀገር ገንዘቦች ክፍያ የሚፈጸም ከሆነ በዕለቱ ከዶላር ጋር ከሚኖረው ምንዛሬ ጋር ተጣጥሞ የሚከፈል ይሆናል።
4. የኢትዮጵያ አርሶና አርብቶ አደሮች የብዝሀ ሕይወት ናሙና ሲወስዱ ከክፍያ ነፃ አገልግሎት ያገኛሉ።
5. ኢንስቲትዩቱ ክፍያ ለሰበሰባቸው አገልግሎቶች ህጋዊ ደረሰኝ መስጠት ይኖርበታል።

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ethiopian Biodiversity Institute

## ክፍል ሶስት

## ስለተግባርና ኃላፊነት

9. **የኢንስቲትዩቱ አስተዳደር ተግባርና ኃላፊነት**
   1. የክፍያ ሥርዓት አተገባበርን በበላይነት ይከታተላል፣ ይገመግማል፤
   2. በአፈጻጸሙ ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶችንና ረቂቅ የክፍያ ተመኖችን ተገቢነት ይገመግማል፣ ውሳኔ ይሰጣል፤
   3. የክፍያ ሥርዓት በሚሻሻልባቸው አግባቦች ላይ ሀሳብ ያቀርባል፣ ውሳኔ ይሰጣል፤
   4. ከክፍያ ሥርዓት ጋር ተያይዞ ለሚያጋጥሙ የአሠራር ማነቆዎች እዲፈቱ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤
   5. እንደ አስፈላጊነቱ ሌሎች በክፍያ ሥርዓቱ ዙሪያ ተያያዥነት ያላቸው ጉዳዮች ሲነሱ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል።
10. **የክፍያ አስፈጻሚ ተግባርና ኃላፊነት**
    1. በዚህ መመሪያ መሠረት ክፍያን ህጋዊ ሥርዓቱን ተከትሎ ተፈጻሚ ያደርጋል፤
    2. በክፍያ ትመናና ትግበራ ዙሪያ ከሚመለከታቸው የተቋሙ የስራ ክፍሎች ጋር በቅንጅት ይሠራል፤
    3. ከአገልግሎት ክፍያ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችን ተከትሎ ተገቢውን ምላሽ ይሰጣል፤
    4. ከአገልግሎት ክፍያ የሚሰበሰበውን ገንዘብ ያስተዳድራል፤
    5. ክፍያውን በአገልግሎትና በተጠቃሚዎች ዓይነት በመለየት ያስፈፅማል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. **ክልከላ**
    1. የዚህን መመሪያ መስፈርትና ሥርዓትን ያልተከተለ ማንኛውንም የክፍያ ተመን በኢንስቲትዩቱ ውስጥ ማስፈጸም እንዲሁም ከተመን ውጪ ማስከፈል የተከለከለ ነው።

ካርታ ካስኬ ካልሳ (ፒኤች.ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

2. ተጠቃሚዎች ክፍያ ለፈጸሙበት አገልግሎት ተጨማሪ ክፍያ ማስከፈል የተከለከለ ነው።

12. <u>ተጠያቂነት</u>

ማንኛውም የዚህን መመሪያ አፈጻጸም የተላለፈ ሰው አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

13. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ለዚህ መመሪያ ተግባራዊነት የመተባበር ግዴታ አለበት፡።

14. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ኢንስቲትዩቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል።

15. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጸደቀበት ከ ሐምሌ 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል።

ዶ/ር ካርታ ካስኬ
ዋና ዳይሬክተር
የኢትዮጵያ ብዝሀ ሕይወት ኢንስቲትዩት
ሐምሌ 2017